# የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፡

# በጎ አድራጎት ድርጅት

# መመሥረት።

ከአበራ ጀምበሬ።

፲፱፻፵፪

www.ethiopianorthodox.org

# የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡

## መ መ ሥ ረ ት ።

ከአበራ ፡ ጆምበሬ ።

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አጤ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡
በኻያ ፡ ዘጠነኛው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡
በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡
ታ ተ መ ።

---

አዲስ ፡ አበባ ፡ ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፤

ለተመሠረተበት ፡ ቀን ፡

የ ተ ሰ ጠ ፡

መ ታ ሰ ቢ ያ ።



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
የድርጅቱ ፡ መሥራች ።

www.ethiopianorthodox.org

# መ ግ ቢ ያ ።

በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡«ከመቀበል ፡ ይልቅ ፡ መስጠት ፡ ይበልጥ ፡ የተቀደሰ ፡ ነው » ፡ ተብሎአል ። የዚህንም ፡ ዋጋ ፡ ተመራምሮ ፡ ማወቅ ፤ ዐውቆም ፡ በልግሥና ፡ መስጠት ፡ ለሰብአዊ ፡ ስሜት ፡ መግለጫ ፡ መልካም ፡ መሣሪያ ፡ ነው።ሰብአዊ ፡ ስሜትም ፡ ይበልጥ ፡ ሊገለጽና ፡ ሊፈጸምም ፡ የሚቻለው፡በበጎ፡ አድራጎት ፡ ሥራ ፡ ነው ።

በዚህም ፡ መንፈስ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ ሀብታቸውን ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ተግባሮች ፡ በመስጠት ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ያቋቋሙ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። ለማስረጃም ፡ ያህል ፡ የአቋቋሙት ፡ ድርጅት ፡ በሚፈጽመው ፡ ሕዝባዊ ፡ አገልግሎት ፡ ስማቸው ፡ በጣም ፡ የተጠራውን ፡ የጥቂቶቹን ፡ አድራጎት ፡ በአጭሩ ፡ ለመግለጽ ፡ እሞክራለሁ ።

የትምህርት ፡ ዝንባሌያቸውና ፡ ሥራቸውም ፡ የሳይንስን ፡ (የሥነ፡ፍጥረትን)፡ጥበብ ፡ መመርመርና ፡ የዕውቀትንም ፡ ውጤት፡ ለኑሮ ፡ ማሻሻያ ፡ ማዋል ፡ የሆነ ፡ አልፍሬድ ፡ ኖቤል ፡ የተባሉ ፡ የስዊድን ፡ ተወላጅ ፡ ራሳቸው ፡ ባወጡት ፡(በፈለሰፉት)፡ ዳይናማይት፡ ንግድ ፡ በጣም ፡ ከብረው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ ጊዜ ፡ ሞታቸው ፡ ሲቃረብ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ሥልጣኔና ፡ ሰላም ፡ እንዲኖር ፡ በማሰብ፡ካለ ፡ ንብረታቸው ፡ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ለቤተ ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ተሰጥቶ ፡ ቀሪው ፡ ጥቅም ፡ በሚያስገኝ ፡ ሥራ ፡ ላይ፡ ውሎ ፡ (አክሲዮን ፡ ተገዝቶበት)፡ ወለዱ ፡ ለኖቤል ፡ ሽልማት ፡ እንዲሰጥ ፡ ስለ ፡ አደረጉ ፡ እንደ፡ ኤውሮፓ ፡ አቈጣጠር ፡ በ፲፱፻፡ ዓ. ም. የኖቤል ፡ ድርጅት ፡ ተቋቋሞ ፡ በያመቱ ፡—

ሀ/ በፊዝክና ፡ በኪሚስትሪ ፡ (በሥነ ፡ ፍጥረት ) ፡

www.ethiopianorthodox.org

ለ/ በሜዲሲን ፡ (በሕክምና ፡ ጥበብ ) ፡
ሐ/ በሊትሬቸር ፡ (በሥነ ፡ ጽሑፍ ) ፡
መ/ በሰላም ፡ ጥበቃ ፡ ትግል ፡

ከፍ ፡ ያለ ፡ሞያ ፡ ላሳዩ ፡ ሰዎች ፡ ሽልማት ፡ ስለሚሰጥ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የመሻሻል ፡ እርምጃ ፡ ሊደረግ ፡ ተችሎአል ።

እንደዚሁም ፡ ሮክፌለር ፡ የተባሉ ፡ አሜሪካዊ ፡ ሀብታም፡ በጎ ፡ መንፈስ ፡ አነሣሥቶአቸው ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ አቈጣጠር ፡ በ፲፱፻፱ ፡ ዓ ም « የሮክፌለር ፡ ድርጅት » ፡ በሚል ፡ ስያሜ ፡ የምግባረ ፡ ሠናይ ፡ ድርጅት ፡ አቋቋሙ ። ይኸውም ፡ ድርጅት ፡ በ፲፱፻፲፫ ፡ ዓ. ም. በሕግ ፡ ስለ ፡ ታወቀ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ከሚገኙት ፡ ታላላቅ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅቶች ፡ አንዱ ፡ ሆኖአል ።

የዚህም ፡ ድርጅት ፡ ዓላማ ፡ በጠቅላላው ፡ ሲነገር ፤ ዕውቀትን ፡ በማጐልመስና ፡ ከዚሁም ፡ የሚገኘውን ፡ መልካም፡ ውጤት፡ ለሰብአዊ ፡ ጥቅምና ፡ ፍላጎት ፡ በሚገባ ፡ በማዋል ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ደኅንነት ፡ ማዳበር ፡ ነው ። ጠቅላላ ፡ ዓላማው ፡ ም ፡ ይህ ፡ ሲሆን ፤ በተለይ ፡ አስተያየት ፡ የተሰጣቸው ፡ ተግባሮች ፡ የሕክምና ፡ ትምህርትና ፡ የሕዝብ ፡ ጤና ፡ አጠባበቅ ፡ ሲሆኑ ፤ እንደዚሁም ፡ የባዮሎጂና ፡ የመድኀኒት ፡ መፈለግን ፤ የእርሻ ፡ ተግባር ፡ መሻሻልና ፡ የሶሺያል ፡ ሳይንስ ፤ የሰብአዊ ፡ ርኅራኄ ፡ ሥራዎችንና ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉትንም ፡ ተግባሮች ፡ ይፈጽማል ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ሄንሪና ፡ ኤድሴል ፡ ፎርድ ፡ የተባሉ ፡ የአሜሪካን ፡ ተወላጅ ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ ወንድማማቾች ፡ በቀና፡ መንፈስ ፡ ተመርተው ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ አቈጣጠር ፡ በ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ. ም. «የፎርድ ፡ ድርጅት»፡ ተብሎ ፡ የሚጠራውን ፡ የበጎ ፡ አድራ



ጎት ፡ ድርጅት ፡ አቋቋሙ።የድርጅቱም ፡ ዓላማ ፡ በአጭሩ፡ለሕዝብ፡ ደኅንነት ፡ ማገልገል ፡ ነው ። ፍላጎቱም ፡ በብሔራዊ ፡ እድገት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የሚያስገኙትን ፡ ተግባሮች፡እየመረጠ ፡ ስለነዚሁ ፡ በሚደረገው ፡ ጥረት ፤ በተለይም ፡ የትምህርት ፡ ባሕሪ ፡ ባላቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ ለሚገጥመው ፡ ችግር ፡ ማቃለያ ፡ የሚረዱትን ፡ ዘዴዎች ፡ ለማግኘት ፡ በሚቻልበት ፡ ረገድ ፡ ሁሉ ፡ ርዳታ ፡ መስጠት ፡ ነው ።

ዐይነተኛው ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ሥራውም ፡ ለትርፍ ፡ ለማይሠሩ ፡ ሌሎች ፡ ድርጅቶችና ፡ አቅዋሞች ፡ ርዳታ ፡ መስጠት ፡ እንጂ ፡ በጥቂት ፡ ሁኔታዎች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ድርጅቱ ፡ ራሱ፡ አዲስ ፡ ጥናት ፡ የመመራመር ፡ የማስተማርና ፡ ይህን ፡ የመሰለም ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ በቀጥታ ፡ አይሠራም ። ሌሎችም ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅቶች ፡ በየአገሩ ፡ ተቋቁመው ፡ ጠቃሚ ፡ አገልግሎት ፡ በመስጠት ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ።

በኢትዮጵያስ ፡ በበጎ ፡ አድራጎት ፡ ሥራው ፡ አስመስጋኝ፡ ሰብአዊ ፡ ስሜቱን ፡ ሊገልጽልን ፡ የቻለ ፡ ማነው ?

በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ አሰጣጥ ፡ ላይ ፡ ከማንም ፡ ይልቅ ፡ ተቀዳሚ ፡ ሆኖ ፡ የሚታወሰው ፡ የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ ነው ። ግርማዊነታቸው ፡ ሕይወታቸውን ፡ ለሚወዱት ፡ ሕዝብ ፡ ደኅንነትና ፡ እድገት ፡ በማዋል ፡ ብዙ ፡ የሥራ ፡ ድርጅቶችን ፡ ለማቋቋም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥረትና ፡ መሥዋዕትነትም ፡ ለማድረጋቸው ፡ ዕድለኛው ፡ የአሁኑ ፡ ትውልድ ፡ የዐይን ፡ ምስክር ፡ ነው ።

ግርማዊነታቸው ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ከመሠረቷዋቸውና፡ ከአቋቋሙዋቸው ፡ ሥራዎች ፡ አንዱ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡

www.ethiopianorthodox.org

የተቋቋመው ፡ « የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት» ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመው ፡ የምግባረ ፡ ሠናይ ፡ ድርጅት ፡ ነው ። የዚህም ፡ ድርጅት ፡ አገልግሎት ፡ ከትውልድ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ የሚተላለፍ ፡ እንዲሆን ፡ በማሰብ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ለዘለቄታ ፡ ነዋሪነቱ ፡ አስተማማኝ ፡ መድን ፡ እንዲሆን ፡ ለዚሁ ፡ ድርጅት ፡ መተዳደሪያ ፡ በቸርነታቸው ፡ የሰጡት ፡ ቻርተር ፡ በሐምሌ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ.ም.በቍጥር ፡ ፲፩ ፡ በወጣው ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ በመውጣቱ ፡ የምሥራቹን ፡ በዚህ፡ድርጅት ፡ ተጠቃሚ ፡ ለሆነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡አበስራለሁ ።

በዚህም ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ለማገልገል ፡ ከአንድም ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ዕድል ፡ ስለ ፡ ተሰጠኝ ፡ ስለ ፡ ድርጅቱ ፡ ሥራ ፡ በቅርብ ፡ ለመከታተል ፡ የቻልኩትንና ፡ ስለ ፡ አላፊ፡ታሪኩም ፡ በመጠያየቅ ፡ የተረዳሁትን ፡ ለሕዝብ ፡ ለመግለጽ ፡ ያህል፡ስለ ፡ ድርጅቱ ፡ መሥራች ፡ ቅን ፡ አሳብና ፡ እንደዚሁም ፡ ስለ ፡ ድርጅቱ ፡ ታሪክና ፡ ዓላማ ፡ በአጭሩ ፡ የምትገልጽ ፡ ይህችን ፡ አነስተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ሳዘጋጅ ፡ አንባቢ ፡ የሚጠቅም ፡ ነገር ፡ እንደሚያገኝባት ፡ ተስፋ ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ነሐሴ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ. ም.

አበራ ፡ ጀምበሬ ።

## መ ቅ ድ ም ።

ከሁሉ ፡ አስቀድሜ ፡ ከኔው ፡ ዐቅመ ፡ ደካማነት ፡ የተነሣ ፡ ሰፊውን ፡ ታሪክ ፡ በአጭሩ ፡ ለመግለጽ ፡ በመሞከሬ ፡ ይቅርታ፡ እንዲደረግልኝ ፡ እየለመንኩ ፤ « የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ መመሥረት ፡ » በሚል ፡አርእስት፡ ለመሥራቹ ፡ ሕዝባዊ ፡ ውለታ ፡ መታወሻ ፡ እንድትሆን ፡ በማለት ፡ የተዘጋጀችውን ፡ በባለታሪኩ ፡ ወይም ፡ በሚገለጸው ፡ ታሪክ ፡ ገናናነት ፡ ሳይሆን ፡ በመጠኑዋ ፡ ብቻ ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ የሆነችውን ፡ ይህችን ፡ መጽሐፍ ፡ በዚህ ፡ የምግባረ ፡ ሠናይ ፡ ድርጅት ፡ ተጠቃሚ ፡ ለሆነው ፡ ሕዝብ ፡ ሳበረክት፤ አንባቢ ፡ ጉድለቱን ፡ አሟልቶ ፡ ግድፈቱን ፡ አርሞ ፡ እንዲመለከታት ፡ ፍጹም ፡ በሆነ ፡ ትሕትና ፡ አበክሬ ፡ አሳስባለሁ ።

ይህን ፡ ታሪክ ፡ ሳዘጋጅ ፡ ያለፉትን ፡ የታሪክ ፡ ድርጊቶች፡ በመግለጽ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ርዳታ ፡ ላደረጉልኝ ፡ ለክቡር ፡ አባ ፡ ሐና ፡ ጅማና ፡ ለክቡር ፡ ብላታ ፡ መርስዔ ፡ ኀዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ።

ደራሲው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## ስለ ፡ መሥራቹ ፡ ቅን ፡ አሳብ ።

ታላቁ ፡ መሪያችን ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መረጭነት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ መሪነት ፡ ከተቀበሉበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ከልብ ፡ የሚወዱት ፡ ሕዝባቸው ፡ ምድራዊም ፡ ሆነ ፡ ሰማያዊ ፡ ሕይወቱ ፡ የተሟላ ፡ የሚሆንበትን ፤ በነፍሱም ፡ ሆነ ፡ በሥጋው ፡ የሚጠቀምበትን ፤ ለራሱም ፡ ተጠቅሞ ፡ ለተፈጥሮ ፡ ወንድሙና ፡ ለተከታዩ ፡ ትውልድ ፡ የበጎ ፡ አድራጎትና፡የጽድቅ ፡ ተግባሮች ፡ አርአያ ፡ የሚሆንበትን ፡ ተግባር ፡ ዘወትር፡ራሳቸው ፡ በተቀዳሚነት ፡ ሠርተው ፡ በመሥራት ፡ እንድንከተላቸው ፡ ምሳሌ ፡ ሆነውናል ።

የበጎ ፡ ምግባር ፡ ቀዳሚ ፤ የታሪክ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ የጽድቅ ፡ ቃለ ፡ ዐዋጁ ፡ በመሆን ፡ የሚጠቅመውንና ፡ የሚያስጠቅመውን ፡ በቅድሚያ ፡ ሠርተው ፡ ሥሩ ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ በገዥነት ፡ የሥልጣን ፡ ትእዛዝ ፡ በኛ ፡ በሕዝባቸው ፡ ላይ ፡ አልጣሉብንም ።

የሕይወት ፡ ታሪካቸውንም ፡ ስናስታውስ ፡ በዚህ ፡ ዐይነቱ፡ የጽድቅ ፡ ሥራ ፡ የተመላና ፡ የተዋበም ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። ግርማዊነታቸው ፡ ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ በፈጸሙትና ፡ አሁንም ፡ በሚፈጽሙት ፡ የበጎ ፡ አድራጎትና ፡ የሕዝባዊ ፡ አገልግሎት ፡ ተግባሮች ፡ ሕዝባቸው ፡ እየተጠቀመበት ፡ እነሆ ፡ ከዚህ ፡ የትውልድ ፡ ዘመን ፤ የጊዜ ፡ ዐረፍት ፡ የታሪክ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ ደርሰናል ።

ግርማዊነታቸውም ፡ በሥራ ፡ ከገለጹልንም ፡ ብዙ ፡ የአርአያነት ፡ ተግባሮች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ፡ ጐልቶና፡

www.ethiopianorthodox.org



ጥንታዊው ፡ የአሰቦት ፡ ደብረ ፡ ወገግ ፡ ገዳም ፡ የሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።



፬/ መምህር ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፤

፭/ መምህር ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፤

፮/ አባ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ፤

፯/ መምህር ፡ ገብረ ፡ አምላክ ፤

፰/ መምህር ፡ መዝገበ ፤

፱/ መምህር ፡ ገብረ ፡ አብ ፡ (አሁን ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ፊልጶስ) ።

፲/ አባ ፡ ቄርሎስ ፡ (አሁን ፡ ሊቀ ፡ ሥልጣናት) ፤

፲፩/ አባ ፡ ዐሥራት ፤

ናቸው ።

፬ኛ/ ግንቦት ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲፮ ፡ ዓ. ም. በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሚገኘውን ፡ የመንበረ ፡ ልዑል ፡ ማርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ።

ለዚሁም ፡ ንጉሣዊ ፡ ቤተ፡ጸሎት ፡ አለቃነት፡የተሾሙ፡—

፩/ አባ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፤

፪/ መምህር ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ (በኋላ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ) ፤

፫/ አለቃ ፡ ሥርግው ፤

፬/ አባ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡

ናቸው ።

፫ኛ/ በታኅሣሥ ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፪ ፡ ዓ. ም. በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ የቅድስት ፡ ሥላሴን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕንጻ ፡ አስጀምረው ፡ በጠላት ፡ ወረራ ፡ ምክንያት ፡ ተቋርጦ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ወደ ፡ ውድ ፡ አገራቸው ፡ ከተመ

www.ethiopianorthodox.org

በገዛ ፡ አገራቸው ፡ መቃብር ፡ ተነፍገው ፡ በዱር ፡ በገደል ፡ ተበ ትኖ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ ሕይወታቸው ፡ ካገራቸው ፡ ሕይወት ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ መሆኑን ፡ ተመልክተን ፡ አሁን ፡ ዐፅማቸው ፡ ከወደ ቀበት ፡ እንዲሰበሰብ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ጊዜን ፡ በጊዜ ፡ ለውጦ ፡ ውለታቸውን ፡ ለመመለስ ፡ ስለ ፡ ፈቀደልን ፡—

ሀ/ ጠላት ፡ አገራችንን ፡ መውረር ፡ በጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ሲከላከሉ ፡ የወደቁ ፡ ጀግኖቻችን ፤

ለ/ ጠላት ፡ አገራችንን ፡ ከወረረ ፡ በኋላ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ ተጋድሎ ፡ ሲያደርጉ ፡ የሞቱ ፡ አርበኞቻችን ፤

ሐ/ በየካቲት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፱ ፡ ዓ. ም. ጠላት ፡ በልዩ፡ ልዩ ፡ ግፍና ፡ ሥቃይ ፡ የፈጃቸው ፡ ሰላማውያን ፡ ሕዝባችን ፤

የእነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ዐፅም ፡ እየተሰበሰበ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ደንበኛ ፡ የዕረፍት ፡ ስፍራ ፡ እንዲሆን ፡ በመንበረ ፡ ጸባዖት ፡ ገዳም ፡ በመሠረትነው ፡ ቦታ ፡ በክብር ፡ እንዲኖር ፡ ካደ ረግን ፡ በኋላ ፡ ለዚሁ ፡ ገዳም ፡ አስተዳደር ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ተያ ይዞ ፡ የሚገኘውን ፡ ደንብ ፡ ፈቅደን ፡ ሰጥተናል ። » የሚል ፡ ነው ።

በዚህም ፡ የግርማዊነታቸው ፡ ቅን ፡ አሳቢነትና ፡ የአገል ጋዮቻቸውን ፡ የድካምና ፡ የተጋድሎ ፡ ዋጋ ፡ ከፋይነት ፡ ዐፅማ ቸው ፡ እየተሰበሰበ ፡ ወደ ፡ መካነ ፡ ዕረፍቱ ፡ እንዲገባ ፡ በተደረ ገው ፡ መሠረት ፡ « አገርህን ፡ ውደድ ፡ ንጉሥህን ፡ አክብር፡ወገ ንህን ፡ ጠብቅ ፡ » በተባለው ፡ ትእምርተ ፡ መልካም ፡ ዜግነት ፡ ተመርተውና ፡ ልባቸውም ፡ በአገር ፡ ፍቅር ፡ ተቃጥሎ ፡ ስለ ፡ ነጻነታቸው ፡ ሕይወታቸውን ፡ መሥዋዕት ፡ ያደረጉት ፡



አርበኞችና ፡ ስደተኞች ፡ እንደዚሁም ፡ ጠላት ፡ በግፍ ፡ የገደላ ቸው ፡ የብዙ ፡ ሰዎች ፡ ዐፅም ፡ በቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ክር ቲያን ፡ ውስጥ ፡ በተዘጋጀው ፡ የክብር ፡ ስፍራ ፡ በየጊዜው ፡ ይገ ባል ።

እንደዚሁም ፡ በአምስቱ ፡ የመከራ ፡ ዓመታት ፡ በአርበኝ ነት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አገልግሎት ፡ የፈጸሙና ፡ ለጠላት ፡ አንገዛም በማለት ፡ ከአገራቸው ፡ ተሰደው ፡ በተቻላቸው ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ አገራቸው ፡ ነጻነት ፡ የደከሙ ፡ ሰዎች ፡ ሲሞቱ ፡ የሚቀበሩበት፡ በዚሁ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ በተለይ ፡ ከተከለለው ፡ የክብር ፡ ስፍራ፡ እንዲቀበሩ ፡ በመደረጉ ፡ የብዙ ፡ አርበኞችና ፡ ስደተኞች ፡ አስከሬን ፡ በተከበረው ፡ ስፍራ ፡ ተቀ ብሮአል ።

በሕይወት ፡ ያሉትንም ፡ ሆነ ፡ የሞቱትን ፡ አርበኞች፡ ስደ ተኞችና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰማዕታት ፡ ሕያው ፡ ሞያ ፡ ታሪክ ፡ የማ ይዘነጋው ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፤ የዛሬውም ፡ ሆነ ፡ ተከታዩ ፡ ትውልድ ፡ የሚኰራባቸው ፡ ናቸው ።

ዐፅማቸው ፡ ከየቦታው ፡ ተሰብስቦ ፡ ወደ፡ መካነ ፡ ዕረፍቱ፡ የገባው ፡ አርበኞች ፡ ስደተኞችና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰማዕታት ፤ እንደዚሁም ፡ በተለይ፡ ለአርበኞችና፡ ለስደተኞች፡ በተከለለው፡ የመቃብር ፡ ስፍራ ፡ የተቀበሩት ፡ ሰዎች ፡ ብዙዎች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፤ ለማስረጃ ፡ ያህል ፡ የጥቂቶቹን ፡ ስም ፡ እንደሚከተለው ፡ አወሳለሁ ።

ሀ/ ዐፅማቸው ፡ ከመካነ ፡ ረፍቱ ፡ ከገባው ፡ አርበኞችና፡ ስደተኞች፤

፩/ ክቡር ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ ደምሰው ፤
፪/ ክቡር ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፤
፫/ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡ አባ ፡ ነፍሶ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ርያርክ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ) ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈውን ፡ መልእክት ፡ (በብዕራቸው) ፡ በእጃቸው ፡ ጽፈው ፡ ልከውላቸው ፡ ነበር ።

«ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፤
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ፡

ከብፁዕ ፡ አባቴ ፡ ከእጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡

<u>ኢየሩሳሌም ።</u>

እንደ ፡ ምን ፡ ሰንብተዋል ። እኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደኅናነን ። እስከ፡አሁንም ፡ ባለነው ፡ አኳኋን ፡ የምናስበው፡ ለናንተ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ወደኛ ፡ ምንም ፡ የሚያሳስብ ፡ የለም ። ይልቁንም ፡ የኛ ፡ እዚህ ፡ መሆን ፡ በየጊዜው ፡ ጀኔብ ፡ በሚደረገው ፡ ስብሰባ ፤ ቢፈቀድልን ፡ የኛ ፡ መሄድ ፡ ባይፈቀድልንም ፡ መልእክተኞቻችንን ፡ መላክ ፡ ለመጣንበት ፡ ጉዳይ ፡ ዋና ፡ ረዳታችን ፡ ስለ፡ሆነ ፡ የፈጣሪያችን ፡ ፍርድ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጉዳይ ፡ እስካጠቃለለልን ፡ ድረስ ፡ እዚሁ ፡ ሆኖ ፡ ማዳመጥ ፡ የሚያስፈልግ ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ተረዳነው ፡ የፈጣሪያችንን ፡ ቁርጥ ፡ እስክናውቅ ፡ ድረስ ፡ በዚሁ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ለመቈየት ፡ ቈርጠናል ።

የእግዚአብሔርም ፡ ቸርነት ፡ ፈቅዶልንና ፡ አሰናብቶን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እስከምንመጣበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ የሃይማኖት ፡ ችግር ፡ እንዳያገኘን ፤ የሚያድጉትም ፡ ልጆቻችን ፡ የሃይማኖታቸውን ፡ መሠረት ፡ እንዳያጡት ፡ አስበን ፤ አንድ ፡ ጽላቱና ፡ አምስት ፡ መነኰሳት ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳትና ፡ መጻሕፍት ፡ ሰጥተውት ፡ ይዞ ፡ እንዲመጣ ፡ አባ ፡ ሐናን ፡ ልኬዋለሁና ፡ ከመምህር ፡ ገሪማ ፡ ጋራ ፡ ተመካከራችሁ ፡ ዐቢይ፡ ጾም ፡ ሳይገባ ፡ እንዲደርስ ፡ አድርጋችሁ ፡ እንድትልኩልን ፡ ይሁን ።



በየጠረፋችንም ፡ ተሰደው ፡ በሰው ፡ ግዛት ፡ ላሉትም ፡ ሰዎቻችን ፡ እንደዚሁ ፡ ሰው ፡ መላክ ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርምና ፡ እየተመካከራችሁበትና ፡ ፈቃዱ ፡ የሚሆን ፡ መነኵሴ ፡ እየመረጣችሁ ፡ እስክናስታውቃችሁ ፡ ድረስ ፡ መጠበቅ ፡ ነው ። »

ብፁዕ ፡ እጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስም ፡ ይህ ፡ መልእክት ፡ እንደ፡ደረሳቸው ፡ በስመ ፡ መድኀኔ ፡ ዓለም ፡ የተጠራ ፡ ጽላት፤ ለቍርባንና ፡ ለጸሎት ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳትና ፡ መጻሕፍት ፡ ጨምረው ፡ ስማቸው ፡ ቀጥሎ ፡ በተጻፈው ፡ መነኰሳት ፡

፩/ በመምህር ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፤
፪/ በአባ ፡ ሐና ፤
፫/ በአባ ፡ ማርቆስ ፤
፬/ በአባ ፡ ኃይሉ ፡ ቡሩክና ፤
፭/ በአባ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡
እጅ ፡ በፍጥነት ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ላኩ ።

እነዚህም ፡ መነኰሳት ፡ ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ደረሱ፡ አንድ ፡ መካነ ፡ ጸሎት ፡ ባርከው ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሕግና ፡ ልማድ ፡ የጸሎትና ፡ የቍርባን ፡ ሥርዐት ፡ ያደርጉ ፡ ጀመር ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ቤተ፡ክርስቲያኑዋ፡«በስደት ፡ ያለች፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ » ተብላ ፡ ትጠራ ፡ ነበር ። በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ « የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጸሎት » ፡ የተባለው ፡

www.ethiopianorthodox.org



በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ የማተሚያ ፡ መኪና ፡ ክፍል ።

፪/ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ ጽጌ ፡ ሻውል ፤
፫/ መምህር ፡ ተክሌ ፡ ዘመናገሻ ፡ ማርያም ፤
፬/ አለቃ ፡ ብሉይ ፡ ተክሌ ፡ ዘሀገረ ፡ ጐንደር ፤
፭/ አለቃ ፡ ታመነ ፡ ዘአማሃራ ፡ ሳይንት ፡

ለ/ አዲስ ፡ ኪዳንን ፡ የተረጐሙ ፤

፩/ ንቡረ ፡ እድ ፡ ተክሌ ፡ ታምራት ፤
፪/ አለቃ ፡ ኀሩይ ፡ ፈንታ ፤
፫/ አለቃ ፡ ለማ ፡ ኃይሉ ፤
፬/ አለቃ ፡ ቀጸላ ፡ ወልደ ፡ መድኅን ፡

ሲሆኑ ፤

ሐ/ ጸሐፊዎቹ ፡ ደግሞ ፤

፩/ አለቃ ፡ የሸዋ ፡ ወርቅ ፡ ቢወጣ ፤
፪/ ደብተራ ፡ ወንድማገኝሁ ፡ አልታዬ ፤
፫/ አቶ ፡ ሣህሌ ፡ ሀብተ ፡ ወልድ ፤
፬/ ደብተራ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ኃይሉ ፡
፭/ ደብተራ ፡ ተሰማ ፡ በድሉ ፤
፮/ ደብተራ ፡ ተክለ ፡ ጻድቅ ፡ ዘደብረ ፡ ሊባኖስ ፡
፯/ ደብተራ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡ ወልደ ፡ ተንሣኤ ፡
፰/ አቶ ፡ ልሳነ ፡ ወርቅ ፡ ወልደየስ ፤
፱/ አቶ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ሽሾ ፤
፲/ አቶ ፡ አበበ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡

ናቸው ።

በዚህም ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ የሚከተለው ፡ የግርማ ፡ ዊንታቸው ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ቃል ፡ ተጽፎበት ፡ ይገኛል ። ቃሉም ፡—

« ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ያጻፍኩት ፡ ታትሞ ፡ ለመ

www.ethiopianorthodox.org



የብርሃንና ፡ ሰላም፡ ማተሚያ ቤት ፡ የጥራዝ ፡ ክፍል ።



ቅድስት ፡ አገራቸው ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ የቀድሞ ፡ ጅምራቸውን ፡ ለማሟላት ፡ ይልቁንም ፡ ከግዕዝ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ያስተረጐሙት ፡ ብሉይ ፡ ከ.ዳንና ፡ አዲስ ፡ ኪዳን ፡ ከእናቱ ፡ ከእብራይስጥና ፡ ከግሪኩ ፡ መጽሐፍ ፡ ( ቴክስት ) ፡ የቃል ፡ ልዩነት ፡ አለው ፡ በመባሉ ፡ የልዩነቱ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲጣራና ፡ አማርኛውም ፡ እንዲስተካከል ፡ ለማድረግ ፡ በየካቲት ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ. ም. አንድ ፡ የሊቃውንት ፡ ጉባኤ ፡ አቋቋሙ ። በዚሁም ፡ ጉባኤ ፡ የኢትዮጵያና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሊቃውንት ፡ ይገኙበት ፡ ነበር ።

በጉባኤው ፡ የነበሩት ፡—

<u>የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፤</u>

፩/ ብላታ ፡ መርስዔ ፡ ኀዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ፡ ( ክቡር ) ፡ — ሰብሳቢ ፤
፪/ ሊቀ ፡ ሥልጣናት ፡ መልእክቱ ፡ (አሁን ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ቴዎፍሎስ ) ፡ — አባል ፤
፫/ አለቃ ፡ መኰሪያ ፡ አብዬ ፡ ሆይ ፡ (አሁን ፡ ንቡረ ፡ እድ ) ፡ — አባል ፤
፬/ አቶ ፡ ተሰማ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡ — አባል ፤
፭/ አቶ ፡ ማርቆስ ፡ አጋጅ ፡ የለው ፡ — አባል ፤
፮/ አቶ ፡ ዮሐንስ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ — አባል ፤
፯/ አቶ ፡ አርአያ ፡ ሥላሴ ፡ ወሮታ ፡ — አባል ፡

ሲሆኑ ፡—

<u>የውጭ ፡ አገር ፡ ሊቃውንት ፡ ደግሞ ፤</u>

፩/ ቄስ ፡ ማቲው ፤
፪/ ሚስተር ፡ ግራሃም ፤

www.ethiopianorthodox.org



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የሰላሌ ፡ ገዥ ፡ በነበሩ ፡ ጊዜ ፡ መሠረቱ ፡ የተጣለውና ፤ የቤተ ፡ ሰሊሆም ፡ ጡረታ ፡ ቤት ፡ በአቅራቢያው ፡ የሚገኘው ፡ ታላቁ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

የቤተ ፡ ሰሊሆም ፡ ገዳም ፡ የመሠረት ፡ ጽሑ ፍ፡ (በደብረ ፡ ሊባኖስ) ።





www.ethiopianorthodox.org

የተሰየመው ፡ የጡረታ ፡ ቤት ፡ በዚሁ ፡ ታሪካዊ ፡ ቀን ፡ አቋቋሙ ።

ይህ ፡ ቀን ፡ ለኛ ፡ ለሕዝባቸው ፡ ያስገኘው ፡ ተስፋ ፡ የነጻነት ፡ ጌታችንን ፡ ሕይወትና ፡ የራሳችንም ፡ መጠቀሚያ ፡ የሆነውን ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ መመሥረት ፡ ጭምር፡ ስለ፡ሆነ ፤ ጥቅሙ ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ቀን ፡ «የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ቀን » ፡ ተብሎ ፡ ሊከበር ፡ ይገባዋል ። ቤቱ ፡ ሰሊሆም ፡ የተባለውን ፡ ቤት ፡ ነዳያን ፡ ሥራ ፡ በማቋቋም፡ክቡር፡ አባ ፡ ሐና ፡ ጅማና ፡ አባ ፡ ወልደ ፡ ኢየሱስ ፡ አባይነህ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥረት ፡ አድርገዋል ። በተለይም ፡ ክቡር ፡ አባ ፡ ሐና ፡ ጅማ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የዚሁ ፡ ገዳም ፡ ( የጡረታ ፡ ቤት ) ፡ አስተዳዳሪ ፡ ናቸው ።

፪ኛ ፤ የማተሚያ ፡ ቤትን ፡ ሥራ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለማስፋፋት፡በማሰብ ፡ መስከረም ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲፬ ፡ ዓ. ም. «ብርሃንና፡ ሰላም» ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራውን ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ አቆሙ ።

ይኸውም ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ከቤተ ፡ ሳይዳ ፡ ሆስፒታል ፡ አጠገብ ፡ « ፩ኛ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ማተሚያ ፡ ቤት » ፤ እንደዚሁም ፡ በሐረር ፡ « ፪ኛ ፡ ከሣቴ፡ብርሃን ፡ የልዑል፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ማተሚያ ፡ ቤት » ፡ ቀጥሎም ፡ በጂማ ፡ « ፫ኛ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ማተሚያ ፡ ቤት » ፡ ተብለው ፡ ይጠሩ ፡ የነበሩትን ፡ ቅርንጫፍ ፡ ማተሚያ ፡ ቤቶች ፡ አቋቁሞ ፡ ነበር ።

የብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ በጀመሪያ ፡ ሲቋቋም፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ የሚተዳደር ፡ ቢሆንም ፡ ከጥላት ፡ ወረራ ፡ በኋላ፡



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ማተሚያ ፡ ቤትን ፡ ሲጐበኙ ።

www.ethiopianorthodox.org



ዘመናዊው ፡ ቤተ ፡ ሳይዳ ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሆስፒታል ።



www.ethiopianorthodox.org

ለዚህም ፡ ሆስፒታል ፡ አስተዳዳሪነት ፡ የተሾሙ ፡—

ሀ/ ወደ ፡ ድርጅቱ ፡ ከመዛወሩ ፡ በፊት ፤

፩/ አቶ ፡ ዳዊት ፡ አብዱ ፤
፪/ አቶ ፡ ለማ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ (አሁን ፡ ክቡር) ፤
፫/ አቶ ፡ ሥዩም ፡ ሞገስ ፤

ለ/ ወደ ፡ ድርጅቱ ፡ ከተዛወረ ፡ ወዲህ ፤

፬/ አቶ ፡ አበራ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፤
፭/ አበራ ፡ ጀምበሬ ፤
፮/ አቶ ፡ ለማ ፡ ግዛው ፤

ናቸው ።

፮ኛ ፡ በችግር ፡ ምክንያት ፡ የሕክምና ፡ እርዳታ፡ ለማግኘት፡ ለተሳናቸው ፡ ዜጎቻቸው ፡ በነጻ ፡ መታከሚያ ፡ እንዲሆን ፡ ሰኔ ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ «የቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሆስፒታል» ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራውን ፡ በተለይ ፡ የድኾች ፡ መታከሚያ ፡ የሆነ ውን ፡ ሆስፒታል ፡ አቆሙ ።

ይህም ፡ ሆስፒታል ፡ በመጀመሪያ ፡ ይካሄድ ፡ የነበረው ፡ በሕዝብ ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ ሚኒስቴር ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን፡ በኅዳር፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት፡ ቦርድ፡ መቋቋም ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡ «የቅዱስ ፡ ጳውሎስ፡ሆስፒታል፡ ቦርድ» ፡ ተብሎ ፡ ይጠራ ፡ የነበረውን ፡ ቦርድ ፡ ለዚሁ ፡ ሆስፒ ታልና ፡ ለሆስፒታሉም ፡ የገቢ ፡ ምንጭ ፡ ለሆኑት ፡ አቋሞች ፡ ሀብት ፡ ማስተዳደር ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ስለ ፡ ሾመው ፡ የሆስፒ ታሉን ፡ አስተዳደር ፡ ቦርዱ ፡ ተረከበ ።

ለዚህም ፡ ቦርድ ፡ አባልነት ፡ በመጀመሪያ ፡ በግርማዊነታ ቸው ፡ የተሾሙት ፡—


ከማቴ፡ብርሃን
ለልብ፡ ጠቢባን
አዲስ አበባ

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ አዘጋጅነትና ፡ አታሚ ነትም ፡ ይታተሙ ፡ ከነበሩት ፡ ጋዜጣዎች ፡ አንዱ ።

www.ethiopianorthodox.org



የቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሆስፒታል ፡
(በተለይ ፡ ለድኾች ፡ መታከሚያ ፡ የቆመ) ።



www.ethiopianorthodox.org

ካው ፡ በሚገባ ፡ ታድሶ ፡ በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶ ፡ ዓ. ም. ሥራ ውን ፡ ቀጥሏል ። የፋብሪካውም ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ምስተር ፡ አልፍሬዶ ፡ ፎሊ ፡ ናቸው ።

፲፪ኛ ፤ ለነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ለመጻሕፍትና ፡ ለጽሕፈት ፡ መሣሪያዎችም ፡ መሸጫ ፡ እንዲሆንና ፡ ገቢውም ፡ ለድርጅቱ ፡ ሥራ ፡ ማስፋፊያ ፡ እንዲውል ፡ ታስቦ ፡ « ብርሃን ፡ የጽሕፈት ፡ መሣሪያ ፡ መደብር » ፡ በሚያዝያ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶ ፡ ዓ. ም. ተከ ፈተ ። የመደብሩም ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ዶክተር ፡ ቫርጋ ፡ ናቸው ።

፲፫ኛ ፤ በታላቁ ፡ ጀግና ፡ በልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ በ፲፰፻፺፰ ፡ ዓ.ም.በሐረር ፡ ከተማ ፡ የተቋቋመው ፡«የልዑል፡ራስ፡ መኰንን ፡ ሆስፒታል» ፡ ለብዙ ፡ ዘመናት ፡ በፈጸመው ፡ አገልግ ሎት ፡ በጣም ፡ የታወቀና ፡ የተመሰገነም ፡ ጥንታዊ ፡ ሆስፒታል፡ ነው ። ይኸውም ፡ ሆስፒታል ፡ በፈረንሳዮች ፡ እጅ ፡ ገብቶ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ከፍሎ ፡ ሆስ ፒታሉን ፡ አስለቀቀ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሆስፒታሉ ፡ በዘመ ናዊ ፡ ዕቅድ ፡ ተደራጅቶና ፡ በሚገባ ፡ ታድሶ ፡ ሕዝባዊ ፡ አገ ልግሎቱን ፡ በበለጠ ፡ እንዲሰጥ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ በተሰ ጠው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ሆስፒታሉ ፡ ተስፋፍቶና ፡ ሙሉ ፡ የሕ ክምና ፡ ድርጅትም ፡ እንዲኖረው ፡ ተደርጎ ፡ የተለመደ፡ አገልግ ሎቱን ፡ ከሐምሌ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ ቀጥሎ ል።ይህም ፡ ሆስፒታል ፡ ወደ ፡ ድርጅቱ ፡ ከመዛወሩ ፡ በፊት ፡ ይካሄድ ፡ የነበረው ፡ በሕዝብ ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ ሚኒስቴር ፡ ነበር።




የመርሐ ፡ ዕውራን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ።

www.ethiopianorthodox.org



በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ተሻሽሎ ፡ የተሠራው ፡ የልዕልት ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ሆስፒታል ፡ (ሐረር) ።



ቃሉም ፡ « ለወጣቶች ፤ ለሽማግሌዎች ፤ ለሕመምተኞች፤ ለአካለ ፡ ስንኩሎች ፤ የአካል ፡ ወይም ፡ የምግባር፡ ተሐድሶ፡ለሚያሻቸውና ፡ የገንዘብ ፡ አቅማቸው ፡ የማይፈቅድላቸው ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ከችሎታቸው ፡ ጋራ ፡ ተመጣጣኝ ፡ የሆነ ፡ ትምህርት ፡ ለማግኘት ፡ ለተሳናቸው ፡ ሰዎች ፡ በሚያደርገው ፡ ርዳታና ፡ በትምህርት ፤ በሳይንስና ፡ በሥነ ፡ ጥበብም ፡ መስፋፋት ፡ ረገድ ፡ በሚያሳየው ፡ አርኣያነት ፡ ለሕዝብ ፡ አስፈላጊ ፤ ለአገር፡ ጠቃሚ ፡ በሚሆኑት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ቀዳሚና ፡ አበረታች ፡ በመሆን ፤ ለምንወዳት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዐይነተኛ ፡ ኀይልና፡ ምግባራዊ ፡ መሪነት ፡ የሚሰጥ ፤ እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ እኛም ፡ የምንወደውን ፡ የሕዝባችንን ፡ የደኅንነትና ፡ የእድገት፡እርምጃ ፡ ለማጎልመስ ፡ በሕይወታችን ፡ ዘመን ፡ ለፈጸምነው ፡ መሥዋዕትነትና ፡ ጥረት ፡ ዘላቂ ፡ መታሰቢያ ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ የበጎ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ለማቋቋም ፡ አስበን ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ አዘናል » ፡ የሚል ፡ ነው ።

ይህም ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ሰብአዊ ፡ ስሜቱን ፡ የገለጸበት፣ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት፡ መመሥረት፡ጽኑ፡ መሠረት ፡ ነው ። ድርጅቱ ፡ የተቋቋመበትን ፡ መንፈስ ፡ ከተረዳን ፡ ዘንድ ፡ የድርጅቱን ፡ ዓላማ ፡ መረዳት ፡ ስለሚጠቅም፡የማወቅ ፡ ግሥጋሤያችን ፡ እንቀጥል ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ድርጅቱ ፡ ዓላማ ።

ድርጅቱ ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ገቢውን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ውሳኔ ፡ የሚሰጥባቸው ፡ ዓላማዎች ፡ ተግባሮችና ፡ አገልግሎቶች ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org



ዘመናዊው ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ሆስፒታል ፡ (ሐረር) ።



፩፤ ሕመምተኞችን ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ ድኩማንና ፡ ዕጓለ ፡ ማውታን ፤ ድኾች ፡ የሆኑ ፡ ወጣቶችን፡ ወይም ፡ ሽማግሌዎችን፤ አካለ ፡ ስንኩሎችንና ፡ ግብረ ፡ መጥፎዎችን ፡ በማሳከምና ፡ ራሳ ቸውን ፡ እንዲረዱ ፡ በማድረግ ፤ በማስታመም ፡ በመጠበቅ፤በማ ስተማር ፤ በመርዳትና ፡ በማበረታታትም ፡ የኢትዮጵያን፡ሕዝብ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ ለማሻሻልና ፡ ድኅንነቱንም ፡ ለማጐልመስ ፤

፪፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱትን ፡ ዓላማዎች ፡ ተግባሮ ችና ፡ አገልግሎቶች ፡ ለመፈጸም ፡ ሲባል፡ የታቀዱ፡ድርጅቶችን፡ ማኅበሮችን ፡ አቋሞችን ፡ በተለይም ፡ የተቸገሩትን ፡ ወጣቶች ንና ፡ የሽመገሉ ፡ ሕሙማንን ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ ድኩማንንና ፡ ግብረ ፡ መጥፎዎችን ፤ እነዚህን ፡ የመሳሰሉትንም ፡ የሚረዱ ትን ፡ የርኅራኄና ፡ የምግባረ ፡ ሠናይ ፡ አቋሞችን ፡ ለማቋቋም ፡ ለማስፋፋትና ፡ ለመርዳት ፤

፫፤ የሰውን ፡ ሥቃይና ፡ በሽታዎችን፡ ለማስወገድና፡የጤና፡ አጠባበቅንና ፡ የጽዳትን ፡ ሁኔታዎች ፡ ለማሻሻል፡ የሚረዱትን፡ የሳይንስ ፡ ምርመራዎችንና ፡ ጥናቶችን ፡ ለማካሄድ ፤ ለመደገ ፍና ፡ ለመርዳት ፤

፬፤ ለአእምሮ ፡ መጐልመስና ፡ ለሥነ ፡ ጥበብ ፡ መስፋፋት፡ ሲባል ፡ የታቀዱ ፡ የሳይንስ ፡ ምርመራዎችንና ፡ ጥናቶችን ፡ ለማቋቋም ፤ ለማካሄድ ፤ ለመርዳትና ፡ ለማገዝ ፤

ይኸውም ፡—

ሀ/ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ኑሮ ፡ በማሻሻል ፡ ወይም፡ በሳይንስ፡ ወይም ፡ በሥነ ፡ ጥበብ ፡ መስፋፋት ፡ ረገድ ፡ አዳዲስ ፡ ዕው ቀት ፡ ወይም ፡ የምርመራ ፡ ውጤት ፡ ለሚያስገኙ ፡ ሽልማት ፡ መስጠትን ፤

ደግሞም ፡—

www.ethiopianorthodox.org



የቤተ ፡ ሰሊሆም ፡ ጡረታ ፡ ቤት ፤ የጸሎት ፡ ቤቱና ፡ ተጠዋሪዎቹ ።



በዘመናዊ ፡ ዐቅድ ፡ የተደራጀው ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ሆስፒታል ፡ (ሐረር) ።

www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ ፡በበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ከሚከናወኑት ፡ ከብዙዎቹ፡ ሥራዎች ፡ ጥቂቶቹ ፡ የሚከተሉ ት ፡ ናቸው ።

ሀ/ በነጻ ፡ መታከሚያ ፡ ሆስፒታሎች ፤

በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ የሚገኘው ፡ ፪፻፶ ፡ አልጋዎች ፡ ያለው ፡ የቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሆስፒታልና ፡ በሐረር፡ከተማ፡ የሚገኘው ፡ ፩፻፲፯ ፡ አልጋዎች ፡ ያለው ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ሆስፒታል ፡ በውስጥ ፡ ታካሚነትም ፡ ሆነ ፡ በተመላላሽነት፡ ለችግረኞች ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ( በነጻ ፡ ) የሕክምና ፡ አገልግሎት ፡ ይሰጣሉ ።

ለ/ ልዩ ፡ የካንሰር ፡ በሽታ ፡ መታከሚያ ፡ ክፍል ፤

አሠቃቂው ፡ የካንሰር ፡ በሽታ ፡ የያዛቸውን ፡ ሕሙማን ፡ ለማከም ፡ የሚያስችል ፡ መሣሪያና ፡ ድርጅት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ በቤተ ፡ ሳይዳ ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሆስፒታል ፡ ብቻ ፡ በመሆኑ ፡ በዚሁ ፡ በሽታ ፡ የተለከፉ ፡ ችግረኞች ፡ እንደ ፡ በሽታቸው ፡ ጽናትና ፡ ቀለልተኛነት ፡ በውስጥ ፡ ታካሚነትም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በተመላላሽነት ፡ የሚታከሙበት፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ በዚሁ ፡ ሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ ተመድቦ ፡ ብዙ ፡ ድኾች ፡ ተገቢውን ፡ ሕክምና ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያገኛሉ ።

ሐ/ የዕውራን ፡ ትምህርት ፤

የዚህን ፡ ዓለም ፡ ብርሃን ፡ ለማየት ፡ ዕድል ፡ ያጡ ፡ ዕውራን ፡ የሚረዱበትንና ፡ በጣት ፡ ዳሰሳም ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የእጅ ፡ ሥራም ፡ መሥራት ፡ የሚችሉበትን ፡ ዕውቀት ፡ የሚገበዩበት ፡ በጠቅላላም ፡ ለወደፊቱ ፡ ራሳቸውን ፡ የሚችሉበትን ፡ ትምህርት ፡ የሚማሩበት ፡ «መርሐ ፡ ዕውራን ፡ » ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለዕውራን ፡ የተመደበውን ፡ ዐይነት ፡ ትምህርት ፡ ይሰጣል ።



በመርሐ ፡ ዕውራን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ዕውራኑ ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ።

www.ethiopianorthodox.org

በግርማዊነታቸውም ፡ ቸርነት ፡ ለዕውራን ፡ የሚያገለግሉ፡ መጻሕፍት ፡ በአማርኛ ፡ በብዛት ፡ ለማሳተም ፡ ይቻል ፡ ዘንድ፡ የብሬል ፡ የማጎተም ፡ መኪና ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መጥቶ ፡ በመርሐ ፡ ዕውራን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በመቋቋም ፡ ላይ ፡ ስለሚገኝ ፡ ለዕውራኑ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተስፋ ፡ ሆኖአቸዋል ።

በዚህም ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከተማሩት ፡ ወጣቶች ፡ መካከል ፡ ጥቂቶቹ ፡ ከዐይናማዎቹ ፡ ተማሪዎች ፡ ጋራ ፡ ከሁለተኛ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ ከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ በመቀጠል ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ። እነዚህም ፡ ተማሪዎች ፡ በገቡበት፡የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከክፍላቸው ፡ አንደኛና ፡ ሁለተኛ ፡ በመሆን ፡ የሚሰጣቸውን ፡ ፈተና ፡ በየጊዜው ፡ ስለሚያልፉ ፡ የመርሐ ፡ ዕውራንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አስመስግነውታል ። ለከፍተኛ ፡ ትምህርትም ፡ ሁለት ፡ ዕውራን፡ ወደ፡ውጭ፡ አገር ፡ ተልከዋል ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ በዚሁ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከሚማሩት ፡ ዕውራን ፡ መካከል ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ በኦፔራሲዮንና ፡ በሌላም፡ ዐይነት፡ሕክምና፡ሊድኑ፡የሚችሉ ፡ መሆናቸው ፡ በሐኪሞች ፡ ምርመራ ፡ ስለ፡ተረጋገጠ ፡ በግርማዊነታቸው ፡ ቸሮታ፡ለልዩ፡ሕክምና፡ ወደ ፡ አሥመራ ፡ ተልከው ፡ ፕሮፌሰር፡ ጐራ፡ከአከሚቻቸው፡በኋላ፡ ከነዚሁ ፡ ሰባቱ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ብርሃን ፡ ለማየት፡በቅተዋል ።

## መ/ የዕጓለ ፡ ማውታ ፡ ማሳደጊያ ፤

የሥጋ ፡ ደዌ ፡ ከያዛቸው ፡ ሰዎች ፡ ለተወለዱ ፡ እናትና፡አባታቸው ፡ በሕፃንነታቸው ፡ ለሞቱባቸውና ፡ አሳዳጊ ፡ ዘመድ ፡ ለሌላቸው ፡ ድኾች ፡ ሕፃናት ፡ ማሳደጊያ ፡ የተቋቋመው ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ድኾች ፡ የሆኑ ፡ ሕፃናትን ፡ በልዩ ፡ ጥንቃቄና ፡ በትምህርት ፡ ተከባክቦ ፡ ያሳድጋል ።



በመርሐ ፡ ዕውራን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከሚማሩት ፡ ዕውራን ፡ ለሕክምና ፡ ወደ ፡ አሥመራ ፡ ተልከው ፡ የነበሩት ፡ ተማሪዎች ። (ከነዚሁ፡ ሰባቱ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ብርሃን ፡ ለማየት ፡ ችለዋል) ።

www.ethiopianorthodox.org

ለ/ የቤተ ፡ ሰሊሆም ፡ ገዳም ፡ የሚገኝበት ፡ ቦታና ፡ በላዩ፡ ላይ ፡ የተሠሩት ፡ ቤቶች ፡ ከነእህል ፡ ወፍጮው ፤

ሐ/ በሰላሌ ፡ አውራጃ ፡ የሚገኝ ፡ በግምት ፡ ዐሥራ ፡ ሦስት፡ ጋሻ ፡ ከሦስት ፡ ሩብ ፡ የሚሆን ፡ የቀላድ ፡ ርስት ፤ በግርማዊነታቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ልግሥና ፡ ለድርጅቱ ፡ ተሰጥቶዋል ።

ግርማዊነታቸው ፡ በቸርነታቸው ፡ ለሚወዱት ፡ ሕዝባቸው ፤ በተለይም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ደዌ፡ ለሚሠቃዩ ፡ ድኾች፡ዜጎቻቸው ፡ አገልግሎት ፡ ለተቋቋሙት ፡ አቋሞች ፡ መርጃ፡ የሚሆኑ ፡ ዝርዝራቸው ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የተመለከተውን ፡ መሬቶች ፤ የከተማ ፡ ቦታዎችና ፡ ቤቶችም ፡ ለድርጅቱ ፡ በርስትነት ፡ ሰጥተዋል ። የግል ፡ ንብረታቸውንም ፡ ለዚህ ፡ የተቀደሰ ፡ ሥራ ፡ እንዲውል ፡ ከማድረጋቸውም ፡ በላይ ፤ ጊዜ ፡ ሳይለዩ ፡ በየሆስፒታሉና ፡ በየትምህርት ፡ ቤቱ፡ እየተገኙ፡ ሕሙማኑን፡ ከማጽናናት፡ ተማሪዎቹን ፡ ከማበረታታት ፡ ቦዝነው ፡ አያውቁም ። እንደዚህ ፡ የሚያስበሉትም ፡ ድርጅት ፡ በሚከተለው ፡ ሁኔታ፡እንዲተዳደር ፡ አድርገዋል ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ድርጅቱ ፡ አስተዳደር ።

በጠቅላላው፡ የድርጅቱ፡ ሥራ፡ የሚመራውና፡ ንብረቱም ፡ የሚተዳደረው ፡ በበላይ ፡ ጠባቂዎች ፡ ቦርድ ፡ የበላይ ፡ ተቈጣጣሪነት ፤ በዲሬክተሮች ፡ ቦርድ ፡ መሪነት ፡ በድርጅቱ ፡ ዋና፡ ዲሬክተር ፡ ሥራ ፡ ፈጻሚነት ፡ ነው ።

### ሀ/ የበላይ ፡ ጠባቂዎች ፡ ቦርድ ፤

በበላይ ፡ ጠባቂዎች ፡ ቦርድ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት፡ የሚሾሙ ፡ ዘጠኝ ፡ አባሎች ፡ ይገኙበታል ። ይኸውም ፡ ቦርድ ፡



ግርማዊነታቸው ፡ ሕሙማንን ፡ ማጽናናት ፡ ስለሚያዘወትሩ፤ በቀዳማዊ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፡ ሆስፒታል፡ አንድ፡ በሽተኛ፡ ኦፔራሲዮን፡ ሲሆን፡ሲመለከቱ።

www.ethiopianorthodox.org

ድርጅቱን ፡ የሚጠብቅና ፡ ሥራውንም ፡ በጠቅላላው ፡ የሚቈ
ጣጠር ፡ ከመሆኑም፡ በላይ ፡ በቻርተሩ ፡ በተሰጠው ፡ መብት፡
መሠረት ፡ ከድርጅቱ፡ የዲሬክተሮች ፡ ቦርድ ፡ የሚቀርብለትን፡
አሳብ ፡ እያጠና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ያደርጋል ። የመጀ
መሪያዎቹም ፡ የበላይ ፡ ጠባቂዎች ፡ ቦርድ ፡ አባሎች ፤

፩/ ልዑል፡መርዕድ፡ አዝማች፡ አስፋ፡ ወሰን፡ ኃይለ፡ሥላሴ፡ የኢትዮጵያ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፤
፪/ ልዕልት ፡ ተናኘ ፡ ወርቅ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አባል ፤
፫/ ልዑል ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የገሙ ፡ ጐፋ ፡ ጠቅላይ ፡ ገዥ ፡ . . . . »
፬/ ልዑል፡ ወሰን፡ ሰገድ፡ መስፍን፡ ሐረር፡ . . »
፭/ ክቡር ፡ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዴንት ፡ . . . . . . . . »
፮/ ክቡር ፡ የጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዴንት »
፯/ ክቡር ፡ የጽሕፈት ፡ ሚኒስትር ፡ . . . . »
፰/ የመንበረ ፡ ጸባኦት ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊቀ ፡ ሥልጣናት ፤ »
፱/ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ዩኒቬርሲቲ ፡ ኰሌጅ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ »

ናቸው ።

### ለ/ የዲሬክተሮች ፡ ቦርድ ፤

የዲሬክተሮች ፡ ቦርድ ፡ ለሦስት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ የሚያገለ
ግሉ ፡ ሰባት ፡ አባሎች ፡ ይገኙበታል ። ከሰባቱም ፡ አባሎች ፡
አንዱ ፡ የድርጅቱ ፡ ዋና ፡ ዲሬክተር ፡ ሲሆን ፤ ሦስቱ ፡ በበላይ ፡
ጠባቂዎች ፡ ቦርድ ፤ አንዱ ፡ በገንዘብ ፡ ሚኒስትር ፤ አንዱ ፡ በሕ



ልዑል ፡ መርዕድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፤
የድርጅቱ ፡ የበላይ ፡ ጠባቂዎች ፡ ቦርድ ፡
ፕሬዚዴንት ።

www.ethiopianorthodox.org

ገዘብ ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ ሚኒስትር ፤ አንዱ ፡ በትምህርት ፡ ሚኒስትር የሚሾሙ ፡ ይሆናሉ ። የዲሬክተሮች ፡ ቦርድ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ከዲሬክተሮች ፡ ቦርድ ፡ አባሎች ፡ መካከል ፡ በበላይ፡ጠባቂዎች፡ ቦርድ ፡ ተመርጦ ፡ ይሾማል ። የዲሬክተሮች ፡ ቦርድ ፡ የድርጅቱ ፡ ቀዋሚ ፡ ሀብት ፡ ባለ ፡ አደራ ፡ በመሆኑ ፡ በቻርተሩ ፡ በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ የድርጅቱ ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ ትርፍና ፡ አገልግሎት ፡ የሚያስገኝበትን ፡ ዘዴ ፡ ለመምረጥና ፡ ንብረቱንም ፡ ለማስተዳደር ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሙሉ ፡ ሙብትና ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶታል ። የዲሬክተሮች ፡ ቦርድ ፡ በዋናው ፡ ዲሬክተር ፡ ሥራ ፡ ጠቅላላ ፡ መቈጣጠር ፡ ከማድረጉም ፡ በላይ ፡ ለድርጅቱ ፡ አስተዳደር ፡ አስፈላጊ ፡መስለው፡ የታዩትን ፡ መምሪያዎችና ፡ መሪ ፡ አሳቦች ፡ ሁሉ ፡ ለዋናው ፡ ዲሬክተር ፡ በየጊዜው ፡ ይሰጣል ።

<u>በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የዲሬክተሮች ፡ ቦርድ ፡ አባሎች ፤</u>

፩/ ክቡር ፡ ሜጀር ፡ ጄኔራል ፡ ሙሉ ፡ ጌታ ፡ ቡሊ ፡ — ሊቀ ፡ መንበር ።
፪/ ክቡር ፡ ብላታ ፡ ትርፌ ፡ ሹምዬ ፡ — አባል ፤
፫/ ክቡር ፡ ብላታ ፡ መርስዔ ፡ ኀዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ፡ — አባል ፤
፬/ አቶ ፡ ዮሐንስ ፡ ጸጌ ፡ — አባል ፤
፭/ አቶ ፡ ውብሸት ፡ ድልነሳሁ ፡ — አባል ፤
፮/ አበራ ፡ ጆምበሬ ፡ ( የድርጅቱ ፡ ተጠባባቂ ፡ ሹም ) ፡ — አባል ፤

ናቸው ።



ሜጀር ፡ ጄኔራል ፡ ሙሉጌታ ፡ ቡሊ ፡
የድርጅቱ ፡ የዲሬክተሮች ፡ ቦርድ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ።

www.ethiopianorthodox.org



የድርጅቱ ፡ የዲሬክተሮች ፡ ቦርድ ፡ በስብሰባ ፡ ላይ ።



### ሐ/ የድርጅቱ ፡ ዋና ፡ ዲሬክተር ፤

ዋናው ፡ ዲሬክተር ፡ በቦርዱ ፡ የበላይ ፡ ተቈጣጣሪነት ፡ የድርጅቱ ፡ ሥራ ፡ ፈጻሚና ፡ አስፈጻሚም ፡ ሹም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ የድርጅቱ ፡ የዘወትር ፡ ሥራ ፡ የሚመራው ፡ በዋናው ፡ ዲሬክተር ፡ ነው ።

አነስተኛው ፡ አገልጋያችሁም ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ የድርጅቱ፡ ምክትል ፡ አስተዳዳሪ ፡ ሆኜ ፡ ከመሥራቴም ፡ በላይ ፡ የድርጅቱ፡ ተጠባባቂ ፡ ሹም ፡ በመሆን ፡ በዚሁ ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የማገልገል ፡ ዕድል ፡ ስለ ፡ ተሰጠኝ ፡ እነሆ ፡ ከኔ ፡ የሚጠበቀውን ፡ አገልግሎት ፡ ለመፈጸም ፡ በአለኝ፡ ዐቅም ፡ ሁሉ ፡ በመጣጣር ፡ ላይ ፡ እገኛለሁ ።

የድርጅቱ ፡ ጠቅላላ ፡ ሥራ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተገለጸው ፡ ሁኔታ ፡ የሚካሄድ ፡ ሲሆን ፤ የድርጅቱ ፡ የገቢ ፡ ምንጭ ፡ የሆኑት ፡ በተለይ፡ የንግድ ፡ መልክ ፡ ያላቸው ፡ አቅዋሞች ፡ ደግሞ ፡ የሚተዳደሩት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ኮርፖሬሺን ፡ ነው ።

የነዚህም ፡ በመቋቋም ፡ ላይ ፡ የሚገኙት ፡ ማኅበሮች ፡ (ኮርፖሬሽን) ፡ የዲሬክተሮች ፡ ቦርድ ፡ አባሎች ፡ ስም ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።

### ሀ/ የግዮን ፡ ሆቴልና ፡ የመካኒዛ ፡ አልኮል ፡ ፋብሪካ ፡ ኮርፖሬሽን ፡ ቦርድ ፤

| | |
|---|---|
| ፩/ አቶ ፡ ከተማ ፡ ይፍሩ ፡ | ሰብሳቢ ፤ |
| ፪/ ምስተር ፡ ሮበርት ፡ ዲ ፡ እስኮት ፡ | አባል ፤ |
| ፫/ አቶ ፡ ተፈሪ ፡ ሻረው ፡ ( በፊት ) ፡ አበራ ፡ ጀምበሬ ፡ ( አሁን ) ፡ | አባል ፤ |

www.ethiopianorthodox.org



ዘመናዊው ፡ የግዮን ፡ ሆቴል ፡ መዋኛ ።



ለ/ የብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ማተሚያ ፡ ቤትና ፡ ብርሃን ፡ የጽሕፈት ፡ መሣሪያ ፡ መደብር ፡ ኮርፖሬሽን ፡ ቦርድ ፤

፩/ አቶ ፡ ተፈሪ ፡ ሻረው ፡ ( በፊት ) ፡
አበራ ፡ ጀምበሬ ፡ ( አሁን ) ፡ — ሰብሳቢ ፤

፪/ አቶ ፡ አርአያ ፡ ዕቁባ ፡ እግዚእ ፡ — አባል ፤
ምስተር ፡ ኢ ፡ መንዚስ ፡ — »

፫/ ምስተር ፡ ፖል ፡ ቬርጊስ፡ (ከአሁን ፡ በፊት) ፡ — »

የድርጅቱ ፡ ሥራ ፡ የሚካሄደው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተገለጸው ፡ ሁኔታ ፡ ሲሆን ፡ ዓላማው ፡ ደግሞ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንደ ተገለጸው ፡ ሁሉ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎትና ፡ ጥቅም ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተገለጸው ፡ ሁሉ ፡ የሕሙማንን ፡ ሥቃይ፡ ለማቃለልና ፡ ተስፋ ፡ ላጡና ፡ ለተቸገሩ ፡ ሰዎች ፡ አሳሳቢ ፡ የሆነውን ፡ የኑሮ ፡ ችግር ፡ ለማቃለል ፡ ዐይነተኛ ፡ መሣሪያ ፡ በመሆን ፡ በጣም ፡ ስለ ፡ ረዳ ፡ መልካም ፡ እርምጃ ፡ የተደረገ ፡ ቢሆንም ፡ ገና ፡ ከግቡ ፡ አልተደረሰም ።

አሁን ፡ ያሉትን ፡ የሥራ ፡ ድርጅቶች ፡ ለማስፋፋትና ፡ ለማደርጀት ፡ እንደዚሁም ፡ ገቢያቸው ፡ ሰፋ ፡ ባለ ፡ መጠን ፡ ድኾችና ፡ ችግረኞችን ፡ ለመርዳት ፡ የሚያስችሉ ፡ አቅዋሞችን ፤ በበለጠ ፡ ሁኔታ ፡ ለማስፋፋት ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ሰፊ ፡ የሥራ ፡ ዕቅድ ፡ በማደራጀት ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

ስለዚህ ፡ በተቻለን ፡ መጠን ፡ እንደ፡እኛ ፡ ያልታደሉትን ፡ ወገኖቻችንን ፡ እንድንረዳ ፡ የጽድቅ ፡ መምህር ፡ የሆኑ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ መንገዱን ፡ እነሆ ፡ መርተውናል ። እንግዲያስ ፡ ለምን ፡ ይህን ፡ የተቀደሰ ፡ አርአያነታቸውን ፡ አንከተልም ?

www.ethiopianorthodox.org




ብርሃን ፡ የጽሕፈት ፡ መሣሪያ ፡ መደብር ።



## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

### ሕዝባዊ ፡ ማኅሰቢያ ።

በሰብአዊ ፡ ርኅራኄ ፡ በኩል ፡ የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ እውነተኛና ፡ የማያቋርጥ ፡ ድካም ፡ የቱን፡ ያህል፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ በተገለጸው ፡ ተረድተናል ።

ከዚህም ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ላስታውስ ፡ የምፈቅደው ፡ ተቀዳሚውና፡ዐይነተኛው ፡ የድርጅቱ ፡ ዓላማ ፡ «ሕመምተኞችን ፡ የዕድሜ፡ልክ ፡ ድኩማንና ፡ ዕጓለ ፡ ማውታን ፡ ድኾች ፡ የሆኑ፡ወጣቶችን ፡ ወይም ፡ ሽማግሌዎችን ፡ አካለ ፡ ስንኩሎችንና ፡ ግብረ ፡ መጥፎዎችን ፡ በማሳከም ፡ ራሳቸውን ፡ እንዲረዱ ፡ በማድረግ ፡ በማሳታመም ፡ በመጠበቅ ፡ በማስተማር ፡ በመርዳትና ፡ በማበረታታትም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ ማሻሻልና ፡ ደኅንነቱንም ፡ ማጐልመስ» ፡ መሆኑን ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ የተገለጸውን ፡ ዓላማ ፡ ሲተነትኑት ፡ የሚከተሉትን ፡ መሠረታዊ ፡ የምግባረ ፡ ሠናይ ፡ አድራጎቶች ፡—

ሀ/ ለሕመምተኞች ፡ የሕክምና ፡ ርዳታ ፡ መስጠት ፤
ለ/ ተስፋ ፡ ያጡ ፡ ደኾችን ፡ በኑሮዋቸው ፡ መደገፍ ፡
ሐ/ ዕጓለ ፡ ማውታን ፡ ማሳደግ ፤
መ/ አካለ ፡ ስንኩሎችን ፡ መርዳትና ፡ ሠርተው ፡ ለማደር ፡ እንዲችሉ ፡ ማድረግ ፤
ሠ/ ግብረ ፡ መጥፎዎች ፡ ጠባያቸውን ፡ እንዲያርሙና ፡ ራሳቸውንም ፡ እንዲረዱ ፡ የተቻለውን ፡ ማድረግና ፡ ሌሎችንም ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ የሥራ ፡ ዕቅዶችን ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ።

www.ethiopianorthodox.org

እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ከፍተኛ ፡ ዓላማ ፡ ያለውንም ፡ ድርጅት ፡ ለማቋቋም ፡ መሥራቹን ፡ ያነሣሣቸውም ፡ ቅን ፡ መንፈስ ፡ ሌላ፡ ሳይሆን ፤ ከግርማዊነታቸው ፡ አገላለጽ ፡ በቀጥታ ፡ በመጥቀስ ፡ እንዳስረዳሁት ፡ ሁሉ ፡ ለሕዝብ ፡ አስፈላጊ ፡ ለአገር ፡ ጠቃሚ ፡ በሚሆኑት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ቀዳሚና ፡ አበረታች ፡ በመሆን ፡ ለሚወዱዋት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጽኑ ፡ ኀይልንና ፡ ምግባራዊ፡ መሪነ ትን፡እንዲሰጥ ፡ በማሰብ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ የዚህ ፡ ሁሉ ፡ አድራጎት ፡ መድረሻ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ ለማሻሻልና ፡ ደኅንነቱንም ፡ ለማጐልመስ ፡ መሆኑን ፡ ተጠቃሚው ፡ ሕዝብ ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ሊገነዘበው ፡ ይገባል ።

በጠቅላላውም ፡ ለሕዝብ ፡ በተለይም ፡ ለችግረኞች፡ ጥቅም፡ ሲባል ፡ ሊፈጸም ፡ የሚገባው ፡ ተግባር ፡ ችግሩም ፡ ሆነ፡ ሥራው፡ ጥቅሙም ፡ ሆነ ፡ አገልግሎቱ ፡ የሁላችንም ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ ትልቅና ፡ ትንሽ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ሳይለይ፡ሁላችንንም፡ የሚመለከት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ «ተከተል ፡ አለቃህን ፡ ተመልከት ፡ ዓላማህን» ፡ በሚለው ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ ለበጎ ፡ አድራ ጎት ፡ ሥራ ፡ ተባባሪ ፡ በመሆን ፤ የተቻለንን ፡ በማድረግና ፡ በመ ለገሥም ፡ ከኛ ፡ የሚጠበቀውን ፡ ፈጽመን ፡ መገኘት ፡ አለብን።

የዚህም ፡ መልካም ፡ ዓላማ ፡ አፈጻጸም ፡ ከሕዝባዊ ፡ ግዴ ታችን ፡ ጋራ ፡ የተያያዘና ፡ ዋንኛውም ፡ ክፍል ፡ በመሆኑ ፡ በሕ ይወታችን ፡ ዘወትር ፡ የሚያጋጥመንን ፡ የተፈጥሮ ፡ ወንድሞቻ ችንና ፡ እኅቶቻችንን ፡ ችግርና ፡ ሥቃይ ፡ እንደ ፡ ራሳችን፡ ችግር፡ በመቍጠር ፡ በመለኮታዊ ፡ በሰብአዊና ፡ በብሔራዊም ፡ ሕግ ፡ የታዘዘውን ፡ ለራሳችን ፡ ሊደረግልን ፡ የምንወደውን ፡ ለሌሎች፡ በማድረግ ፡ የርኅራኄና ፡ የኀዘኔታ ፡ ሥራ ፡ ሠርተን ፡ መገኘት ፡ ተገቢያችን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ግዴታችንም ፡ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

ይህንንም ፡ ተግባር ፡ የበጎ ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የግዴታም ፡ አድርጌ ፡ ለመግለጽ ፡ በመሞከሬ ፡ ከመሥመር ፡ እንደ ፡ ወጣሁ ፡ ይቈጠርብኝ ፡ ይሆናል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለሌሎች፡ማሰብና ፡ የሌሎችን ፡ ችግርም ፡ ማቃለል ፡ ዐይነተኛው፡ የመልካም፡ ዜጋ ፡ ተግባር ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ ይህ ፡ አድራጎት ፡ የፈቃድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የግዴታም ፡ ጭምር ፡ መሆኑ ፡ ስለማይካድ ፡ ያለብንን ፡ ኀላፊነት ፡ ማስታወሴ ፡ ከድፍረት ፡ ሊቈጠርብኝ ፡ አይገባም ። ይህም ፡ ተግባር ፡ መልካም ፡ ዜጋ ፡ ሊፈጽመው ፡ የሚገባ ፡ አስጠቃሚ ፡ ሥራ ፡ መሆኑ ፡ አይካድም ።

መልካም ፡ የአገር ፡ ዜጋ ፡ የሚያስገኘውም ፡ ለሰዎች፡ሁሉ፡ ደኅንነት ፡ ስንል ፡ የዘወትር ፡ ተግባራችን ፡ የፋንታችንን ፡ በመስጠትና ፡ የተቻለንን ፡ በማድረግ ፡ መንፈስ ፡ የተመራ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ መልካም ፡ ዜጋ ፡ ሲባል ፡ ከአንድ ፡ ሰው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ እስከ ፡ ሕዝቦች ፡ ቤተ ፡ ሰብነት ፡ ድረስ ፡ ባለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በማኅበር ፡ ተግባሮች ፡ በሚገባና ፡ በአስተዋይነት ፡ ተካፋይ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ ሰው ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ የመልካም ፡ ዜግነት ፡ መሠረቱ ፡ ለብቻ ፡ መኖር ፡ አለመቻሉን፡በመገንዘብ፡ለገዛ፡ ራስ ፡ የማለትን ፡ ስሜት ፡ ቀንስ ፡ አድርጎ ፡ ለቤተ ፡ ሰብ ፤ ለጎረቤት ፤ ለአገር ፡ ሰው ፤ በጠቅላላውም ፡ ለሰብአዊ ፡ ፍጡር፡ ሙሉ፡ የሆነ ፡ ሕይወት ፡ እንዲኖር ፡ ማሰብ ፡ ይገባል ።

ይኸውም ፡ ለሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ማኅበራዊ ፡ መብቶችና ፡ ፍላጎቶች ፡ አስተያየት ፡ ማድረግ ፡ እንደሚገባን ፡ መሠረታዊ ፡ የሆነ ፡ አሳብ ፡ የሚሰጠን ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። የሌሎችን ፡ ማኅበራዊ ፡ መብቶችና ፡ ፍላጎቶች ፡ ተገንዛቢ ፡ የመሆን ፡ ቀና ፡ መን



ፈስ ፡ የሚገኘው ፡ ለሰብአዊ ፡ ፍጡር ፡ ሁሉ ፡ መልካም ፡ ሕይወትን ፡ ከመመኘት ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ማኅበራዊ ፡ ስሜት ፡ አለው ፡ ለሚባል ፡ ዜጋ ፡ በማንኛውም ፡ ሁኔታና ፡ ጊዜም ፡ ሰብአዊ ፡ ዋጋን ፡ ከማንኛውም ፡ ነገር ፡ ማስበለጡ ፡ የመልካም ፡ አሳቢነቱ ፡ ደገኛ ፡ ምልክት ፡ መሆኑን ፡ ሊዘነጋው ፡ አይገባውም ።

ይልቁንም ፡ ከሦስቱ ፡ ዐቢይ ፡ ብፅዕናዎች ፡ አንዱ ፡ ስለ ፡ ሆነው ፡ ስለ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ (ስለ ፡ ፍቅር) ፡ ከተጻፉት ፡ ጽሑፎች ፡ ሁሉ ፡ በአዲስ ፡ ኪዳን ፡ «የድኾች ፡ እጅ ፡ የሀብታሞችን ፡ ቤት ፡ ይሠራል» ፡ ተብሎ ፡ ከተነገረው ፡ መለኮታዊ ፡ ቃል ፡ የበለጠ ፡ አጥጋቢና ፡ አስጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ስለማይገኝ፡ በኑሮ፡ ለተጐሳቈሉትና ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ ላልታደሉት ፡ ሰዎች ፡ የተቻለንን ፡ በማድረግ ፡ ምድራዊና ፡ ሰማያዊ ፡ ተግባርን ፡ አጣምሮ ፡ ለመፈጸም ፡ የሚያስችል ፡ የተሻለ ፡ ዘዴና ፡ መንገድም ፡ ስለ ፡ ማይገኝ ፡ ይህንኑ ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ ለመጠቀም ፡ መጣጣር፡ ይገባል ። በጎ ፡ ፈቃድም ፡ ካለ ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ መፈጸም ፡ ለማንም ፡ የሚያዳግት ፡ አይሆንም ።

ድርጅቱም ፡ በቅን ፡ መንፈስ ፡ የተሰጠ ፡ ማንኛውንም ፡ ዐይነትና ፡ ማንኛውንም ፡ ያህል ፡ ስጦታ ፡ ድጋፍ ፡ ወይም ፡ ችሮታ ፡ በደስታ ፡ ስለሚቀበል ፡ አነሰ ፡ ወይም ፡ ጠበበ ፡ ሳንል ፡ ሁላችንም ፡ እንደየዐቅማችን ፡ በመስጠት ፡ ከኛ ፡ የሚጠበቀውን ፡ የመልካም ፡ ዜግነት ፡ ተግባር ፡ ፈጽሞ ፡ ለመገኘት ፡ ያብቃን ።

እንደዚሁም ፡ ከአሁን ፡ በፊትም ፡ በጎ ፡ መንፈስ ፡ አነሣሥቶዋቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ ያበረከቱትን ፡ ሰዎች ፡



www.ethiopianorthodox.org



"ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴና ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን፤
(በተለመደ ፡ ቸርነታቸው ፡ ይህን ፡ ሰፊ፡ልግሥና ፡ ያደረጉልን) ።



ረት ፡ የያዘ ፡ ቻርተር ፡ በመስጠት ፡ የልደት ፡ በዓላቸውን ፡ ለሕዝብ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ስጦታ ፡ መስጫ ፡ አድርገውት ፡ መዋላቸውን ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በዚች ፡ ትንሽ ፡ መጽሐፍ ፡ መደምደሚያ ፡ ላይ ፡ ደግሜ ፡ የማሳስበው ፤ የግርማዊነታቸውን ፡ አርአያነት ፡ በመከተል ፤ እያንዳንዳችን ፡ በነፍስ ፡ ወከፍ ፤ በመታደል ፡ ረገድ ፡ ከኛ ፡ ዝቅ ፡ ብለው ፡ የሚታዩትን ፡ ወገኖቻችንን ፡ የመርዳት ፡ ተግባር ፡ እንዳለብን ፡ ባለመዘንጋት ፡ ለተቸገሩ ፡ ተስፋ ፡ ላጡና፡ ለሚሠቃዩ ፡ ወንድሞቻችንና ፡ እኅቶቻችን ፡ ደኅንነት ፡ ስንል ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅትን ፡ በመደገፍ ፡ በዚህ ፡ የተቀደሰ ፡ ተግባር ፡ ሁል ፡ ጊዜም ፡ ተባባሪና ፡ ተሳታፊ ፡ ሆነን ፡ እንድንገኝ ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ ፈጽሞ ፡ ለመገኘት ፡ አምላክ ፡ ይርዳን ።

www.ethiopianorthodox.org

| ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አ ር እ ስ ት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| | ሐ/ የዕውራን ፡ ትምህርት ፤ | ፻፪ |
| | መ/ ዕጓለ ፡ ማውታን ፡ ማሳደግ ፤ | ፻፬ |
| | ሠ/ ጠቅላላ ፡ የጤና ፡ አጠባበቅ ፡ አገል ግሎት ፤ | ፻፯ |
| | ምዕራፍ ፡ ፯ ። | |
| ፲፰ | ለድርጅቱ ፡ ስለ ፡ ተሰጡ ፡ ንብረቶች ፤ | ፻፯ |
| | ሀ/ ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሆስፒታል ፤ | ፻፯ |
| | ለ/ ለቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሆስፒታል ፤ | ፻፱ |
| | ሐ/ ለልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ሆስፒታል ፤ | ፻፲፩ |
| | መ/ ለቀ.ኃ.ሥ. የዕጓለ ፡ ማውታ ፡ ት/ቤት ፤ | ፻፲፩ |
| | ሠ/ ለመርሐ ፡ ዕውራን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፤ | ፻፲፫ |
| | ረ/ ለድርጅቱ ፡ በቀጥታ ፤ | ፻፲፫ |
| | ሰ/ ለቤተ ፡ ሰሊሆም ፤ | ፻፲፫ |
| | ም ዕ ራ ፍ ፡ ፰ ። | |
| ፲፱ | ስለ ፡ ድርጅቱ ፡ አስተዳደር ፤ | ፻፲፬ |
| | ሀ/ የበላይ ፡ ጠባቂዎች ፡ ቦርድ ፤ | ፻፲፬ |
| | ለ/ የዲሬክተሮች ፡ ቦርድ ፤ | ፻፲፮ |
| | ሐ/ ዋና ፡ ዲሬክተር ፤ | ፻፳፩ |
| | መ/ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ኮርፖሬሺን ፡ የዲሬክ ተሮች ፡ ቦርድ ፤ | ፻፳፩ |
| ፳ | ሕዝባዊ ፡ ማሳሰቢያ ፤ | ፻፳፰ |
| ፳፩ | ማ ጠ ቃ ለ ያ ። | ፻፴፩ |


www.ethiopianorthodox.org